የምንጠይቀው ስለሚያገባን ነው

AMHARIC

# አማርኛ

ወደ CHCO የሚመጣ እያንዳንዱ ታካሚ ጥሩ እንክብካቤ የማግኘት መብት አለው። ስለ እያንዳንዱ ልጅ በተሻለ ሁኔታ ለማወቅ ያስችለን ዘንድ ስለ ዘር፣ ጎሳ፣ ማንነትና ቋንቋ የተመለከቱ ጥያቄዎችን እንጠይቃለን። እርስዎ የሚሰጡን መልሶች ለልጆች የምናደርገውን እንክብካቤ እንድናሻሽል ይረዱናል። **የምንጠይቀው ስለሚያገባን ነው።**

## ስለ ዘር፣ ጎሳ፣ ማንነትና ቋንቋ የተመለከቱ ጥያቄዎችን የምንጠይቀው ለምንድን ነው?

ሁሉም ሰው የራሱ ልዩ ማንነት አለው። እርስዎ የሚሰጡን መልሶች እያንዳንዱ ሰው በግሉ የሚፈልገውን እንክብካቤ ማግኘቱን እንድናረጋግጥ ይረዳናል። እነዚህ ጥያቄዎች ለሚከተሉት ይረዱናል፦

- ለባህል ፍላጎቶችዎና እሴቶችዎ ጥንቃቄ እንድናደርግ
- እንክብካቤን የሚያሻሽሉ አገልግሎቶች እንድናቀርብ
- ለእርስዎና ማህበረሰብዎ ድጋፍ የሚያደርጉ ፕሮግራሞች እንድናዘጋጅ
- የህግ ደረጃዎችን እንድናከብር

## መረጃውን የሚያየው ማን ነው?

ይህን መረጃ የሚያዩት የምዝገባ ሰራተኞች፣ የእርስዎ የእንክብካቤ ቡድን፣ የሆስፒታል አስተዳዳሪዎች እና የጥራት ማሻሻያ ቡድን አባላት ብቻ ናቸው። መረጃው የህክምና መዝገብዎ አካል በመሆኑ ምክንያት ጥበቃ የሚደረግለት የጤና መረጃ ነው።

## መረጃውን የምትፈልጉት ለምንድን ነው?

ይህ መረጃ ለእርስዎም ሆነ ለቤተሰብዎ የተሻለ እንክብካቤ እንድናደርግ እና በእጅጉ በሚፈልጉን ወቅት የሚቻለውን ምርጥ ተሞክሮ እንድናቀርብልዎ ይረዳናል። ለምሳሌ የልጅዎ ተመራጭ ቋንቋ እንግሊዘኛ አለመሆኑን ካወቅን ተርጓሚ ማግኘት የምንችል መሆኑን ማረጋገጥ እንችላለን። ይህ መረጃ በተጨማሪም ስለምናከመው ማህበረሰብ የበለጠ እንድናውቅ ይረዳናል። እርስዎ የሚሰጡን መረጃ ጥቅም ላይ የሚውለው በኮሎራዶ የህጻናት ሆስፒታል ውስጥ ብቻ የምናቀርባቸውን አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች ለማሻሻል ነው።

## መመለስ ባልፈልግ ምን ይሆናል?

ያሳውቁን እና ጥያቄዎን አክብረን ይህን ማስታወሻ እንይዛለን። ሀሳብዎን ከቀየሩ መረጃውን በማንኛውም ጊዜ በMyChart ላይ ሊያሻሽሉ ወይም ለቡድን አባል ሊያሳውቁ ይችላሉ።

Children's Hospital Colorado
*Here, it's different.*™

© Children's Hospital Colorado 2023 All rights reserved. Children's Hospital Colorado complies with applicable Federal civil rights laws and does not discriminate on the basis of race, color, national origin, age, disability, or sex. • ATENCIÓN: si habla español, tiene a su disposición servicios gratuitos de asistencia lingüística. Llame al 1-720-777-1234. • CHÚ Ý: Nếu bạn nói Tiếng Việt, có các dịch vụ hỗ trợ ngôn ngữ miễn phí dành cho bạn. Gọi số 1-720-777-1234. HR-594067L-2023-02